# የቀድሞ ፕሬዝዳንት የአገዛዝ ዘመን አነሳስና ውድቀት እና የፕሬዝዳንቱ የስደት ሕይወት

## ታጠቅ መንጂ (9April 2016)

የዜና ወኪል - SBS (ኣውስጥራሊያ)

ኣስተናጋጅና ጠያቂ -ጋዜጠኛ ካሳሁን ሰቦቃ

ቃለተጠያቂ (ኢንተርቪዊ) - ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀኝ እና ደራሲ ገነት አየለ

25ማርች 2016፤10-11 PM በአውስትራሊያ ሰዓት

ከላይ በተጠቀሰው ዕለትና ሰዓት-በዚህ አርእስት ሥር የተጠየቁትን ጥያቄዎችንና መልሳቸውን በጽሞና አዳምጪያቸዋለሁ። ከተነሱት በርካታ ጥያቄዎችና መልሶች ውስጥ፤ በሚከተሉት ጥቂቶችን ትችት መሰንዘር እፈልጋለሁ።

**ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀኝ የመንግሥቱ ኃይለማርያምን የአገዛዝ ዘመን 'አውንታዊ ቅርሶች' ሲያሥረዱ ፤ መንግሥቱ "በተፈጥሮ ብሩህ አእምሮ የነበረው ፣ አስተዋይ ፣ሰሚ ጆሮ የነበረው ፣ ተናግሮ የሚያሳምን ሰው ነበር ፤ 'ተናግሮ አሣማኝ እንደነበረ ፍሳሃ ደስታና ፍቅሬ ወግድረስ በመጽሐፎቻቸው የጻፉትን አንብቤአለሁ'፤ አሸንፎ የወጣም በዚሁ ችሎታው ሳሆን አይቀርም" አሉ ። በዚህ በአንድ ቅርጫት ውስጥ ያስቀመጥኳቸውን ፕ/ገብሩ ለመንግሥቱ ሃ/ማርያም የመሰከሩትን አውንታዊ አስተያየቶች ወይም እይታዎች ፤ 'ሚዛንአዊነታቸውና ኢሚዛንአዊነታቸውን' እየነጠልኩ ለመተቸት እሞክራለሁ ።**

### ብሩህ አእምሮ

- **የዚህ ሃረግ ሳይንሳዊ ትርጉም ወደጎን ትቼ በማኅበራዊና በጽሑፍ (ሊትራሪ) አማርኛችን ብሩህ አእምሮ ያለው/ያላት ስንል ፤ ብልህ፣ ብልሃተኛ፣ ፈጥኖ ማስብ የሚችል/የምትችል፣ቀና መንፈስ ያለው/ያላት ወዘተርፈ ትርጉሞች ይኖሩታል። የኦክስፎርድ የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት (Oxford English Dictionary- (bright mind- shining; brilliant; cheerful; quick witted etc. በማለት ይገልጸዋል ), google (an enlightened, illuminated ; open minded etc.) በማለት ይገልጸዋል።**

አስተዋይ

- አገናዛቢ፣ አርቆ አሳቢ፣ የቅርቡና የሩቁን የሚያይ/የምታይ፣ግራና ቀኝ የሚመለከት/የምትመለከት፣ የሚያጠፋውና የሚያለማውን የሚያውቅ/የምታጠፋውና የምታለማውን የምታውቅ ወዘተርፈ።

መንግሥቱ ከላይ የተገለጹትን ዓይነት የአእምሮ /የጭንቅላ መስክ (mind faculty) ከነበራቸው/ካላቸው እንዴት ያን ያህል ሕይወት ሊያጠፉ ቻሉ? መንግሥቱ ኃይለማርያም የ(14፣15፣16 ዕድሜ ያላቸው ሕጻናት ከእናቶቻቸ ው ጉያና እቅፍ ተነጥለው እንዲገደሉ ትእዛዝ የሰጡ ሰው አይደሉምን? ከ እነዚያም አንዱ እ.አ.አ (4 Feb 1977 ከሌሎች 26 ወጣቶች ጋር በ 14 ዓመቱ የተገደለው<ባብሌ ሃይለስላሴ>ነው።ልጆቻችሁን የተደበቁበትን፣ መሳሪያ የደበቁበትን፣የኢሕአፓ ጽሁፍ የደበቁበትን ወዘተርፈ አልተናገራችሁም በሚል ሰበብ ፤ ሴትና ወንድ አዛውንቶችን፣ሽማግሌ አባቶችና አሮጊት እናቶችን እንዲገደሉ የፈቀዱ ሰው አይደሉምን? የገደሏቸን ዜጎቻቸውን ሬሳ የሸጡ ፍጹም አረመኔ መሪ አልነበምን?በአንድ ቤት ስድስት ልጆቻቸውን ያጡ ወላጆች እንደ ነበሩ አውቃለሁ ።እኔም አስተዋይና ብሩህ አእምሮ ያላቸው ሰዎች ሁሉ ፍጹም ናቸው ፤ አይሳሳቱም ለማለት አልደፍርም። ነገር ግን አስተዋይና ብሩህ አእምሮ ያለው ሰው ፤የመንግሥቱን ዓይነት ሥህተት አይፈጹምም ባይነኝ ።ምኑ ላይ ነው የበረሁት? ምኑ ላይ ነው ያስተዋሉት? ለመንግሥቱ ብሩህ አእምሮነትና አስተዋይነት ከሰጡናቸው አጼ ቴድሮስና አጼ ምኒሊክ ምን ልንላቸው ነው? ይህ ከእውነት የራቀ (offbeat) ተክለ ብሩህነትና ተክለ አስተዋይነት አሆንምን? መልከጥፉ በስም ይደግፉ ዓይነት አይሆንምን?

ፕሮፌሰር ገብሩ ብሩህ አእምሮነትና አስተዋይነት የሁሉም ፋሽስቶች ባህሪ ነው ማለታቸው ይሆን? ያ ከሆነ -ሂተለር፣ እስታሊን፣ ጀነራል ፍራንኮ፣ ሞሰለኒ ፣ፒነቾት፣ ፖልፖት፣ስኋርቶ፣ ኢዲያሚን ወዘተ.. አስተዋይና ብሩህ አእምሮ የነበራቸው መሪዎች ነበሩ ማለታቸው ይሆን? መንግሥቱ ከእነዚህ ሁሉ የተለዩ ነበሩ/ናቸው፤ ነገር ግን ድርብርብ ወይም ስንጥቅ ማንነት (multiple or split personality) ስላላቸው ብሩህ አእምሯቸውና አስተዋይነታቸ ውን እንዳይሰራ ተጫናቸው (imposed by pre-

determined personality disorder) ማለታቸው ይሆን? አንዳንድ አስተዋይና ብሩህ አእምሮ ያላቸው መሪዮች ፋሽስት ሊሆኑ ይችላሉ ማለታቸው ይሆን? አስተዋይና ብሩህ አእምሮ ያላቸው ሰዎች ሕዝባዊ ባህሪ የላቸውም ፤ ከእነዚም ውስጥ አንዱ መንግስቱ ናቸው ማለታቸው ይሆን?

ሰሚ ጆሮ የነበረው

ይህ ማለት ምን ማለት ነው? በማኅበራዊና በጽሑፍ አማርኛችን ምንን ያመለክታል? ይህ ማለት እኔ ያልኩት ብቻ የማይል፤ የሌሎችን ሃሳብና ምክር ለመስማት የተዘጋጀ/ች፤ የሌሎችን ችግር የሚገባው/ገባት፤ ለሌሎች አዛኝ ወዘተርፍ ትርጉሞች ያሉት ይመስለኛል። ታዲያ ሌላ መንግሥቱ ካልሆነ በሥተቀር፤ እኛ የምናውቃቸው መንግሥቱ የዚህ ዓይነት ስብዕና ነበራቸውን? ፕሮፌሰር ገብሩ– መንግሥቱ 'ሰሚ ጆሮ የነበረው' ሲሉ መንግሥቱ ሕዝባዊ ገጽታ ነበራቸው ማለታቸው ይሆን ? እርሳቸው  መስማት ስለሚፈልጓቸው ነገሮ  ብቻ ማለታችው ይሆን? ፋሽስቶች ሁሉ ስለሚጠቅማቸው ነገር ጆሮዋቸውን ሹክ አድርገው የማዳመጥ ችሎታ አላቸው ማለታቸው ይሆን?

መንግሥቱ ተናግሮ የሚያሳምን ሰው ነበር

አንድን ሰው ወይም መሪ ተናግሮ ማሳመን ይችላል/ትችላልች ስንል ፤ ለውይይት በቀረቡ አጀንዳዎች፣ ነጥቦች፣አርእስቶች ወዘተርፈ ጭብጥ ማስረጃዎች (objective facts) በማቅረብ ሥልጡን (civil) በሆነ መንገድ ተከራክሮ ሌሎችን ማሳመን ሲችል/ስትችል ነው።  መንግሥቱ ሃ/ማርያም መሠረታዊ የክርክር መተክሎችን (principles) ተጠቅመው ፤ ተከራክረውና ተወያይተው፤ በማሳመንና በማመን (by dialogu,fact/s, by force of reason, by persuation and conviction) ጉዳዮችን/ችግሮችን የመፍታት ፣ ፖሊሲዮችን የመቀስ - ችሎታና ባህሪ የነበራቸው መሪ ነበሩን? ተናግሮ የሚሳምን መሪ በራሱ ይተማመናል፤ ተናግሮ የሚያሳምን መሪ የሕዝቡን ጥያቄ በውይይት ይፈታል፤ ተናግሮ የሚያሳምን መሪ በውይይት ያምናል ።

ለምን ነበር ከዕሩብ ምሊዮን የሚበልጡ -ኢትዮጵያ መተኪያ የማታገኘላቸ ው ፍጹም ሕዝብና አገር ወዳድ -ወጣት፣ ጎልማሳና አዛውንት ምሁራን በክላሽኮቭና በመትረየስ ጥይቶች የመተሩት/የረፈረፉት ? ለምን ነበር በአሠሯችው ዜጎቻቸውን ላይ ያን ዓይነት ሰቆቃ የፈጸሙት? ለምን ይሆን ከኢትዮጵያውያን ሕይወት የጥይት ዋጋ ተወደደ የተባለበት? ? ?

ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ለማስፈን፤ ሁሉንም የማህብረሰባችን ዘርፍ - የመምህራን ፣ የሠራተኛ ፣የሃይማኖት፣የከፍተኛ ትምኅርት ተቋማት ወዘተርፈ ያሳተፈ፣ 'በክብ ጠረጴ ወይይት ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይመሠረት' በመጠየቁ  አይደለምን ያ ሁሉ እልቂት የተከተለው? ለምን ተናግረውና ተወያይተው በማሳመን ሥልጣን አይረከቡም ነበር?

የያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥቱን የሚያውቃቸው -በድንፋታቸው፣ በስሜታዊነታቸው፣ ተጽፎ የተሰጣቸውን በቃልአጋኖ ማንበባችውን፣ ውቃቤ/ዛር እንዳለበት ሰው -ያሳረዷቸውን ዜጎቻቸውን ደም ወይም ቀይ ቀለም በጠርሙስ ሞልተው መሥቀል አደባባይ ላይ ማፈንዳታቸውን፣ በወገን ስቃይ የሚደሰቱ፣ የሚሥቁና የሚፈነጥዙ (sadistic and narcissistic) ወዘተርፈ ሰው እንደነበሩ ነው ።

ፕሮፌሰር ገብሩ ተግሮ የሚያሳምን ሲሉ - መንግሥቱ የኤንግልስን ኢንደክቲቭና ዲዳቲቭ ሎጅክ (inductive and deductive logic ),Stella Cottrell`s Effective Analysis and Argument, Stephen Toulmin`s – Claim,Support and Warrant etc.) ዓይነት የክርክር ናሙናዎች ተጠቅመው የመከራከርና የማሳመን እውቀትና ችሎታ ነበራቸው/አላቸው ማለታቸው ይሆን? መንግሥቱ ጥሩ ፕሮፓጋንዲስት ነበሩ ማለታቸው ይሆን? ተናግሮ የማሳመንና የፋሽስታዊ ፕሮፓጋንዳ ልዩነት ባለማወቃቸ ው ይሆን? ፕሮፓጋንዳ የፋሽስቶች ሁሉ ባህሪ መሆኑን ባለማወቃቸው ይሆን?

በአሸናፊነት የወጡትም  በዚሁ ችሎታቸው ሳይሆን አይቀርም ፤ ተናግሮ አሳማኝ እንደነበረ -ፍሳሃ ደስታና ፍቅሬ ወግደረስ በመጽሐፎቻቸው የጻፉትን አንብቤአለሁ - ስላሉትን በተመለከተ

እውነትም መንግሥቱ ሃ/ማርያም የ109ኙ የደርግ አባላት ቁንጮ የሆኑት ተናግሮ በማሳመናቸውን? ብውይይት ሥርዓቶችና አሳማኝ ሃሳቦችን በማፍለቅ በልጠው በመገኘታቸውን፤ በውይይት እንተማመን በማለታቸው፤ የደርግ ቁንጮ -በመቀጠልም የኢትዮጵያ ገዢ ሊሆኑ የበቁት? በሥውር በአደራጅዋቸው ገዳዮች (squads) ተጠቅመው ፈጣንና ተምዘግዛጊ ገዳይ በመሆናቸው አልነበረምን? አማን አንዶምን፣ ተፈሪ ባንቲን፣ አጥናፉ አባተን ወዘተርፈ ከገደሉ በኃላ ፤ "ለምሳ ሲያስቡን ቁርስ አደረግናቸው! "በማለት አልነበረምን ያቅራሩትና የፎከሩት? (የሊቀ መምበር ማዎ መፈክር ተውሰው) ። ታዲያ የት ላይ ነው ተናግሮ አሳማኝነታቸው ? ፍሳሃ ደስታና ፈቅሬ ወግደረስ ከመንግሥቱ ጋር አብረው የተጓዙት መንግሥቱ በሚያቀርቡላቸው አሳማኝ ምክንያቶች ወይም አሳቦች ተገዝተው (governed) ሁነው ሳይሆን፤ ሥልጣንና ምቾት ስለፈለጉና ፍርሃት ስለአዣበበባቸው ነበር ።

ሥልጣን ፦ ፍሳሃ ደስታና ፍቅሬወግደረስ ከመንግሥቱ ጋር ለ17 ዓመታት ኢትዮጵያን ለመግዛት ካስቻላቸው ምክንያቶች አንዱ ሥልጣን ስለፈለጉ ነበር ። የሥልጣን ትርጉም፣ አሉታዊና አውንታዊ ባህሪዮች/ገጽታዎች ከዚህ ንዑስ አርእስት ጋር አዛምዶ መተንተኑ ወደጎን ትቼ ፤ሥልጣን ቁሳቁሳዊ ሃብት (material wealth) ፣ የተደላደለ ኑሮ፣ ምቾት ፣ቅንጦት ወዘተርፈ ያስገኛል ፤ያስፈነድቃል ።ስለሆነም መንግሥቱ በነበራቸው ግዙፍ ሥልጣን ፍሳሃ ደስታና ፍቅሬወግደረስ የሥልጣን አጋሮቻቸውን ሁነው እንዲቆዩና ሥልጣን ያስገኘላቸውን የተንደላቀቀ ሕይወት እንዲኖሩ ዋስትና (security) ሰጥቷቸው ነበር የሚኖሩት ።

ፍርሃት ፦ ፍሳሃ ደስታና ፍቅሬ ወግደረስ ከመንግሥቱ ጋር ለ17 ዓመታት አብረው ኢትዮጵያን የገዙት -ለመንግሥቱ በመበርከክ (by surrender or by being capitulated) ፤ መንግሥቱን ያሉትን ሁሉ ተቀብለውና አሚን ብለው ነው የተጓዙት ። ቢፈራገጡ ፤ ቢከራከሯቸውና ቢሟገቷቸው- የሚከተላቸው ወይም የሚጠብቃቸው ጥይት መሆኑን ያውቁ ስለነበረ ። የቅኝ አገዛዝ እጅግ በጣም አስከፊ ገጽታ - የአእምሮ ቅኝነት ( mind colonization) ነው ።በቅኝ ተገዥዎች- በፍርሃትና በጭንቀት እንዲኖሩ ማድረግ ፣ የማያስብ እንስሳ ነን ብለው እንዲያምኑ ማድረግ ፤ ቅኝ

ገዥዮቻቸውን ፈጣሪያቸው አድርገው እንዲያዩ ማድረግ  ወዘተርፈ ። “አካላቸውን ቀጥቶ ማኅበረሰብ/ሰዎችን ከመቆጣጠር - በጣም ጠቃሚው ዘዴ አእምሯቸውን መቆጣጠር ነው -Controlling the mind is a more effective means of social control than punishing the body” (Michel Foucault).

1)መንግሥቱም በሥልጣን አጋሮቻቸውን አእምሮ ተመሳሳይ ይሁንታ (ፍርሃት) ስለፈጠሩ -ለእነሱ  ፈጣሪያቸውም ፣ ገዢያቸውም ፣ ምሁራቸውም ወዘተርፈ መንግሥቱ እንድሆኑ ተቀበሉ ፤አመኑ (2) የሥልጣን ጥምና የተንደላቀቀ ቁሳቁሳዊ ሕይወት (highly privileged material life) አስማምቶና አቆራኝቶ ኢትዮጵያን እንዲገዙ አደረጋቸው እንጂ መንግሥቱ ‘ተናግሮ የማሳመን’ ችሎታ ስለነበራቸው አይደለም ። ስለሆነም ፍሳሃ ደስታና ፈቅሬወግደርስ ዋሸተዋል፤ ፕ/ገብሩም ተሳስቷል እላለሁ ።

ስለመንግሥቱ ሃ/ማርያም ስደት ሕይወት ከገነት አየለ ጋር

SBS ፡- የቀድሞ ፕሬዝዳንት ስለአገራችው በስደት ሕይወት ላይ ሁነው በምጸት ሲመለከቱ የአገራቸውን ሁኔታ በምን መልኩ ነው የሚረዱት?

ገነት አየለ፡- “መንግሥቱ ከሚታወቁበት ሁኔታ አንዱ በአገር ወዳድነታቸው  ነው ፤ ጠላቶቻቸውም ወዳጆቻቸውም የሚስማሙበት ነው ፤ የአገር ናፍቆትና ፍቅር አሁንም  በልባቸው ይነዳል” ።አገር ወዳድ ሲባል -የኢትዮጵያ መልካምድር ማለት ነውን? የኢትዮጵያ ወንዞች፣ ተራሮች ፣ አራዊት ወዘተርፈ ለማለት ነውን ? ፀረ ሕዝብ ተኩኖ፣ ሕዝብን/ዜጎችን ጨፍጭፎ አገር ወዳድ መሪ መባል ይቻላልን? ምዕምናኑን ሳይሆን ደብሩን፣ ተማሪዎችን ሳይሆን ትምህርት ቤቱን፣ ከብቶቹን ሳይሆን የግጦሽ ሜዳውን ውዘተርፈ  መውደድ እንደ ማለት አይሆንምን?

- በዘመናዊ ትምህርት ዓይኑን የከፈትውንና የነቃውውን -ለሕዝቡ፣ ለአገሩ፣ለባህሉ፣ ለቋንቋው ፣ለአዲስ ሥርዓት፣ ለለውጥ ፣ ለዲሞክራሲ ፣ለመብት፣ለእኩልነት ወዘተርፈ ዘብ የቆመውን ወጣት መመንጠር አገር ወዳድ መሪ ያስብላለን?
- የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኮራባቸውና የአገራችን አለኝታ የነበሩ 60 ጀነራሎች በአንድ ምሽት መግደል አገር ወዳድ ያሰኛልን ? በተለይም ኢትዮጵያ በዚያ ቀውጢ ሁኔታ በነበረበት ወቅት

- በካድሬዎቻቸውን አቃጣሪነት በጦር ግዳጅ ላይ የተሰለፉትን መኮነኖችን ማዕረግ በመቀስ በመቁረጥ ማዋረድና ሞራል መግደል አገር ወዳድነት ነውን?
- ከአገር ጠላት የሚፋለም -ጀግና ፣ደፋር፣ ወኔ፣ሞራል፣ አሞት ወዘተርፈ ያለው ወጣት እንዳይኖር መግደል፣አሥሮ ማሰቃየት፣ ማሳደድ፣ቅስም መስበር ወዘተ.. የአገር ወዳድ መሪ ሚና ነውን?
- ማነው ለውያኔ በር ከፍቶ በሕዝባችንና በአገራችን ላይ ለደረሰው ቀውስ የዳረገን? ያጋለጠን?
- ማነው ተትኪ ለሕዝብና ለአገር የቆመና ተቆርቋሪ የፖለቲካ ድርጅት እንዳይኖር ያደረገው?
- አገርና ሕዝብ ለጠላት አጋልጦ ሰጥቶ መሸሽ አገር ወዳድ መሪ ያሰኛልን?

የአገር ወዳድ መሪ መስፈርቶች እነዚህ ናቸውን? አዎን ጅብና ውሻ በበሉበት ይጮሃሉ ይባል የለምን? አብሯውቸው የበሉ፣የጠጡ፣ የፈነጠዙ የረሸኑና ያስረሸኑ፣ የገደሉና ያስገደሉ አገር ወዳድ መሪ ይልዋቸው ይሆናል፤ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ፋሽስቱ ፣ሰው በላው፣ ፈሪዩ ወዘተ.. መሪ ይላቸዋል ።

SBS ፦ የቀድሞ ፕሬዝደንት ከዚህ በኋላ ወድ አገራቸው የመመለስ እድል አይኖራቸውም፤ ሃ/ሥላሴ ቢሰደዱም  ተመልሰው መጥተው አገራቸውን መርቷል፤ ....ለምን ቴድሮስ አልሆኑም?

ገነት አየለ፦ “ ተገድጄ ነው ከአገር የወጥሁት፤ በመሬት ላይ የነበረው ሁኔት አስገድዶኝ ነው የወጣሁት፤ ሳላውቀው ዙምባቤ ተገኘሁ ነው የሚሉት” ። በዚህ ትምህርተ ጥቅስ  ወስጥ ያሰፈርኳቸውን የገነት አየለን መልሶችእየነጠልኩ መንግሥቱ ምን ለማለት እንደፈለጉ መጠየቅ(interrogate)ማድረግ እፈልጋለሁ ፤

ተገድጄ ነው ከአገር የወጣሁት፤ ማነው ያስገደዳቸው? የኢትዮጵያ ሕዝብ? ምኒስትሮቻቸው?ምዕራባውያን? የሶሻሊስት አገሮች? ለምን አይገልጹትም?

በመሬት ላይ የነበረው ሁኔታ አስገድዶኝ ነው የውጣሁት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ አከ እትፍ ብሎ ስለጠላኝ ማለታቸው ይሆን? የኢትዮጵያ መሬት ስለጠላኝ ማለታችው ይሆን? ወያኔዎች ቤተመንግሥቴ ለመወረስ እየገሰገሱ በመምጣት ላይ ስለነበሩ ማለታቸው ይሆን? ለምን አይገልጹትም?

ሳላውቀው ዞምባቤ ተገኘሁ፤ በጣም የሚገርሞ ይህ አባባላቸውን ነው ፤በድንገት የጎርፍ ውሃ ዞምባቤ ወስዶ ጣለኝ ማለታቸው ይሆን?ማይታወቁ ስውር ሃይሎች (UFO-unidentified objects) ወስደው ዞምባቤ ጣሉኝ ማለታቸው ይሆን?አውሎ ነፋስ አንጠልጥሎ ወስዶ የዞምባቤ ዋና ከተማ ሃረሬ ቁጭ አደረገኝ ማለታቸው ይሆን? ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የመንግሥቱን ሽሽት-በዕቅድና በቅድመ ዝግጅት እንደሆነ ነው የሚያውቀው ። ይኸወም-አጎታቸው ካሳ ከበደን በዞምባቤ የኢትዮጵያ አንባሳደር ማድረግ፣ ቤተሰባቸውን አስቀድሞ መላክ፣ምኒስትሮቻቸውን አስልፈውና ጨብጠው መሰናበታቸውን ወዘ..ማስረጃዎች ናቸው ።

SBS:- የቀድሞ ፕሬዝዳንት ሦሥት መጽሐፍት ለአንባቢያን ለማስነበብ ያሰቡ ሰለሆነ በእነዚህ መጻሃፍታቸውን እውነቱን ያወጡ ይሆን? ማለት እንዴት እንደሸሹ፤ ለዚህ ጥያቄ ገነት ምን እንደመለሰች በትክክል ስለላዳመጥኩ እንዳለ እተወዋለሁ ። ያምሆነ ይህ መንግሥቱ ሶስት ተጨማሪ መጽሃፍት ለመጻፍ ያስገደዳቸው ምን ይሆን? ውሸት በመከመር ተቀባይነት አገኛለህ ብሎ በማሰብ ይሆን? የኢትዮጵያ ሕዝብ ያማያወቀ ሚስጥር ለማጋለጥ ይሆን? ውሸት ደርድረው ብረ ለመሰብሰብ ይሆን? በሕዝባቸው ላይ የፈጸሙትን ግፍ ተናዘው ይቅርታ ለመጠየቅ ይሆን? ይህ ከሆነ ብቻ ነው የእርሳቸውን መጽሃፍት የማነበ ው ካልሆነ ጊዜ ማቃጥል ነው ።

ፕሮፌሰር ገብሩና ገነት አየለ መንግሥቱ የማይገባቸውን ማንነትና የሌላቸውን ተክለሰውነት ሊሰጧቸው ሞከሩ ባይነኝ ። “ብሩህ አእምሮ፣ አስተዋይ፣ ሰሚ ጆሮ የነበራቸው፣ ተናግሮ የሚያሰሙ ፣አገር ወዳድ ...ሰው ነበሩ” ካልን አጼ ቴድሮስና ዳግማዊ ምኒልክ ምን ልንላቸው ነው? ታሪክ ማዛባት አይሆንምን?